# “ሺ ይሙት የሺጥላ አይሙት”

## አንዳንድ ነጥቦች በህወሓት ታሪክ ዙሪያ

በአለምአቀፍ የህዝቦች ፀረ ጭቆና ተጋድሎ ማህደር ላይ ወርቃዊ በሆኑ ቃላት ይሰፍር ዘንድ አሁን ላይ ሆኖ ሲታሰብ ተአምር በሚያስብል ገድል የተሰራው የ17 ዓመቱ የህወሓት የትጥቅ ትግል በአግባቡ አልተሰነደም አለ የሚባለውም መልከብዙ ሰነድና ህያው ግለታሪክ መጪውን ትውልድ ሊያግዝ በሚችል መልኩ ታሪካዊነቱ ሚዛናዊቱ ዙርያመለስነቱና በተለይም ከዘመን ጋር በተቆራኘ መልኩ አስተማሪቱን አካቶ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እስከአሁን ድረሰ ለህዝብ እንዳልቀረበ የሚያከራክር አይደለም::

እንደየሁኔታው በተናጠልና በተደራጀ መልኩ በግልና በድርጅት ደረጃ አቅም በፈቀደ መጠን በተለያየ መልኩ እየወጣ ያለው የህወሓት የታሪክ ስብርባሪም ቢሆን በጣም ጥቂት ናቸው ከሚባሉት ስራዎች በስተቀር የተሰራውንና የሆነውን ያክል በሚመጥን መልኩ አልተሰራም:: አስፈላጊ ጥናታዊ ማተርያላዊና የአቅጣጫ መርህ ድጋፍ ሳያገ«ና የታሪኩን እሴት ከመጪው ትውልድ ጋር ባላስተሳሰረ መልኩ እየተዋቀረ ለስነ ውበታዊነቱም በቂ ግምት በማይሰጥ መልኩ እየቀረበ ያለ በመሆኑ ጠቀሜታው እየተሰራ ነው ያስብል እንደሁ እንጂ ገዝፎ የሚታይ አይደለም::

ይህም በመሆኑ ዘመን ዘመንን እየተካ በሄደ ቁጥር ይህ በታጋይ ህዝቦች ደም ተፅፎ በአእላፍ ሰማእታት ያንንምበረከክም ወኔ ተደጉሶ የተሰራው ድንቅ ታሪክ ደብዛው እየጠፋና ወደ አፈታሪክነት እየተቀየረ ይገኛል:: ዘመን አሃዙን በደመረ ቁጥር እንደ ፍጡር በማይበለትተውና ወትሮም በፅናት ቅብብሎሽ ህያውነቱን እያስመሰከረ በመሄድ ላይ ባለው የህወሓት መስመር ምህዋር ላይ የተሰራው ይህ ድንቅ ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፍም እየተደነቃተፈ ይገኛል::

የሺዎች ሰማእታት አደራ እጻር ላይ አድርሶ ቅርሱን ለትውልድ ለማቀበል! እፎይታ ሳያምረው የትላንቱ የታሪክ ሰው አሁንም ቢሆን ግምባር ቀደም ስፍራ ይዞ ታሪክ እየሰራ ይገኛል:: አሁንም መስመር አሁንም ቃለ ህዝቡን አንግቦ ቀን በቀን ተአምር የሚያሰብል ስራ እየሰራ የብዙሃን ብሄር ብሄረሰቦች ሃገር የሆነችው ኢትዮጵያ አይታው የማታውቀውን እጻዲስ የታሪክ ምእራፍ ሲከትብ ይስተዋላል::

የሃያሉ መስመር ህያውነት የራእያቸውን ብርሃን አደፍርሶ ያጨለመባቸው ግትሮች በበኩላቸው በታሪክ ማህደር ላይ ያጡትን ደማቅ ድል ለማካካስና ሞትን ገድለው በሞቱ ሰማእታት የደመቀችውን ዝሃ ብርሃን ለመበረዝ በብዕር አውድማ ላይ የቃላትና የአረፍተነገር ስለት ሰብቀው

ያልነበረን ነበረ ያልሆነውን ሆነ የነበረውን አልነበረም የሆነውን አልሆነም የሚሉ ድርሳናት ነገን ለሚረከበው አዲስ ትውልድ በማስረከብ ላይ ይገኛሉ::

የእሳት ወላፈን እየለበለበው ያለንባትን ደቂቃ ህያው ያደረገ ህዝባዊ የህወሓት ወታደር! ለሰብአዊ መብት ነበርና የተዋደቀው ማንም ይሁን ማንም የመሰለውን ሃሳብ ሕግና ስርዓቱን አክብሮ በፈለገው የብራና አይነት ቢከትብ እሰየው ከማለት ውጪ ሌላ ምን ይባላል:: አሁንም አሁንም እሰየው ነው:;

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታድያ አዲሱ ትውልድ ህወሓትን መጠየቅ ጀምሯል:: እናም መልስ ይፈልጋል:: በፀረ ድህነቱ ተጋድሎ ላይ ጥያቄዎቼን እመልስ ዘንድ! እማር እመራመር ዘንድ! ይሆን አይሆን« እለይ ዘንድ !ተሰራ ተደረገ የተባለውን ታሪካችሁን ከዘመን ጋር አስዘምናችሁ አቅርቡል« ማለት ከጀመረ ከራረመ::

ታድያ የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ! ህወሓት እንደ ድርጅትና !ተጋዳላይም እንደ ግለሰብ ያን የመሰለ ድንቅና ሃቅ ታሪክ አግባብ ባለው መልኩ ተሰንዶ በተለያዩ የሚዲያ ፎርማቶች ለተተኪው ትውልድ እንዲዳረስ ሃላፊነቱን ባግባቡ መወጣት ለምን አቃተው?

ይህ ጥያቄ የመስመሩን ዘልአለማዊነት ለሚመና የማትጠፋዋን ቀንዲል ከሰማእታት ወንድምና እህቶቹ ለተረከበ ታጋይ ዜጋ በርግጥም ፈታንና እንቅልፍ የሚነሳ አፋጣNG ምላሽ የሚሻ ጥያቄ ነው:; ካለፉት ዓመታት ተሞክሮዎቹ በቂ ትምህርት ቀስሞ የህይወት ጀምበር ሳትጠ ልቅበት ባለድርሻ ነNG ባይ ሁሉ ድርሻውን በማበርከት ጥያቄውን የመመለስ ግዴታ አለበት::

ታሪክ መፃፍ ችሎታን ይጠይቅ ይሆናል:: ታሪክ መፃፍ ብቃትን ይጠ ይቅ ይሆናልዕዕ ታሪክ መፃፍ ብዙ ነገሮችን ይጠይቅ ይሆናል:: ከሁሉም በላይ ግን ታሪክ የድርጊቶችን ሃቅነት ከሌላ ድርጊት ጋር ያለውን ንፅፅር የሚመዝን ሚዛናዊ መነፅርና ዛሬ ላይ ሆኖ ትላንትን ለነገ የሚያስረክብ ሃቀኛ መስመርን መከታ ያደረገ ደልዳላ አመለካከትን ይጠይቅ ይመስለኛል:: እንዲህ አይነቶቹ ፀሃፍት ተፈልገው ይታጠሉ ብሎ መገመት የዋህነት ይመስለኛል::

ከዘመን ጋር መዘመን አልቻለም እንጂ! በዲጂታል ፎርማት ተሰንዶ ፈላጊው ዘንድ በፍጥነትና በጥራት ይደርስ ዘንድ አልቻለም እንጂ:: መቀሌ ሰማእታት ሃወልት ግቢ በከተመው የህወሓት ዶኪሜንተሽን ክፍል ውስጥ ያለው የፅሁፍ የኦድዮ የቪድዮና የፎቶ አእላፍ ሰነድ እንደ መነሻ ሰንቱን ስራ ባቃለለ ነበር::

በእርግጥ የህወሓት ታሪክ የህዝብ ታሪክ ነው:: ህዝብ ደግሞ እንደ ጊዜ ዘልኣለማዊ አይደለም:: እናም በርካታ የታሪክ ሰዎቸ ጊዜ ጥጋግ ላይ

እየደረሱ ከሰሩት ታሪክ ጋር ወደ መቃብር እያዘገሙ ይገኛሉ:: በድንገት ያለፉና እያለፉ ያሉትን ሳይጨምር:: ይህ ጉዳይ ደግሞ የዚህን ሰራ ውስብስብነት እጅጉን ያጎላዋል::

በትግርኛ አንድ አባባል አለ “ሽሕ ይሙት ፅላል ሽሕ አይሙት” ይላል::::ሺ ይሙት የሺጥላ አይሙት እንደማለት ነው ታድያ ተወደደም ተጠላም ሺዎች ሞተዋል ሺዎችም እየተከተሉ:: የህዝብ ታሪክ ግን ጥላ ነውና መሞት የለበትም:: ታሪክ ሲሞት በእድሜአችን አይተናል! ታሪክ በሃያል ተጋድሎ ብርታት እንደገና ሲነሳም እንዲሁ:: እ ታድያ ማናችንም ብንሆን የዚህ ታሪክ አካል ነንና ታሪክ እንደ ሩር ወዲህና ወዲያ እየተንከላወሰ እንዲሞት መፍቀድ የለብንም:: ህያው የህወሓት ታሪክም ህያውነቱን እንደያዘ እስከወዲያኛው ይኖር ዘንድ ድርሻችንን ለማበርከት ሁላችንመ በፅናት እንነሳ::

ቀለበት ቃልአሚን
ከማህደር ተራ
መቀሌ

በዚህ ጉዳይ ላይ ኣሰተያየት ካላችሁ Qalqal2001@gmail.com